Ethiopian Academy of Sciences
የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ

# የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ

## 3 ኛው የሳይንስ ኮንግረስ ጋዜጣዊ መግለጫ

### የወጣቱን አቅም ለዘላቂ የአገር ልማት

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ 3 ኛውን የሳይንስ ኮንግረስ #የሕዝብ ቁጥርን አወቃቀር ያገናዘበ የዕድገት ዕቅድ$ በሚል መሪ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ኅዳር 28 እና 29/2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የስብሰባ አዳራሽ ያካሄዳል።

ወደ 100 ሚሊዮን እየተጠጋ ያለው የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር አገሪቱን ከአፍሪካ ግዙፍ ህዝብ ካላቸው አገራት መካከል እንድትሆን እያደረጋት ይገኛል። ዕድሜው ለሥራ የደረሰው የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እየሰፋና እያደገ የመጣ ሲሆን በያዝነው ምዕተ-ዓመት መጨረሻም አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥሩ 240 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይተነበያል። በመሆኑም ይህ ቁጥር መሠረታዊ የስነ-ሕዝብ አወቃቀር ሽግግር እያደረገ ስለሚሄድ ከዓለም-አቀፋዊና አገራዊ ነባራዊ ሁኔታው በመነሳት በአግባቡ ለዘላቂ ልማት መጠቀም የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ከዚህ መሠረተ-ሀሳብ በመነሳት 3 ኛው ኮንግረስ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት በጉዳዩ ላይ ምክክር ያደርጋል። ኮንግረሱ ከሚንስትሮች፣ ከፖሊሲ አውጪዎች፣ ከተመራማሪዎች፣ ከአጋር አካላት፣ ከዓለም-አቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ ከሲቪክ ማህበረሰቡ እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ጋር በጥልቀት ውይይት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ይመክራል። በዘርፉ ጥናት ያደረጉና ተግባራዊ ሥራዎችን ሲሠሩ የቆዩ ምሁራንም በመረጃ ላይ የተደገፉ የጥናት ውጤቶችንና ልምዶችን ለጉባዔው በስፋት ያቀርባሉ።

የኢትዮጵያን የሕዝብ ቁጥር አወቃቀር ሽግግርና ቀጣይ ተስፋዎች ዳሰሳ፣ አሁን የሚስተዋለውን የስነ-ሕዝብ መዋቅርና ትሩፋቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየት፣ የስነ-ሕዝብ ትሩፋትን እና መዋቅራዊ ለውጡን የፖሊሲ አውጪዎች አጀንዳ ማድረግ እና በመረጃ ላይ የተመረኮዙ አካባቢያዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማመላከትና መጠቆም በዋናነት ዋና ዋና የኮንግረሱ ግቦች ናቸው።

በተያያዥነትም ኮንግረሱ በሁለት ቀናት ቆይታው የተሻሻለ የስነ-ተዋልዶና ሌሎች የጤናው ዘርፍ አገልግሎት አቅርቦቶች፣ ጥራት ያለው ትምህርትና ክህሎት እና የሴቶችና የወጣቶችን የሥራ ዕድል ማጠንከር እንዲሁም አቅም ማጎልበት ዝርዝር ንዑሳን ርዕሰ-ጉዳች ሲሆኑ፤ ጉባዓው በጥልቀት ተወያይቶ ሳይንሳዊ አቅጣጫዎችን በማሳየት ለአገሪቱ ዘላቂ ዕድገት የበኩሉን ያበረክታል ተብሎ ይጠበቃል።